በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እና የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

የቤት ሽያጭ ዋጋ ተመን አሰራር እና የታክስና አገልግሎት ክፍያ ማንዋል ቁጥር 01/2016 ዓ.ም

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ማህደርና ሪከርድ
የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

አዲስ አበባ

2016 ዓ.ም

መግቢያ

በይዞታ አግልግሎትና መብት ፈጠራ ደንብ ላይ የስመ ንብረት ዝውውር አሰራር በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን የቤት ሽያጭ ዋጋ ተብሎ በገዥና ሻጭ መካከል የሚደረግ ውል ላይ የሚቀርበው ዋጋ እጅግ በተገነነ መልኩ ዝቅተኛ በመሆኑ እና በባለሙያ የሚወሰድ የቤት ግምት ዋጋ ወቅታዊ ባመሆኑ መንግስት ከቤት ሽያጭ ተገቢውን ገቢ እየሰበሰበ አልነበረም። በመሆኑ ይህንን ችግር ለመፍታት እንዲቻል ሰኔ 8/2015 ጀምሮ ተግባረዊ የሚደረግ ወቅታዊ የቤት ሽያጭ ዋጋ ተስተካክሎ ተግባራዊ ሆኗል። ይሁን እንጂ በከተማ ደረጃ ተጠንቶ ተግባራዊ የተደረገ የቤት ሽያጭ ዋጋ እና አሰራሩ ላይ ከህብረተሰቡ በርካታ ቅሬታዎች እየቀረቡ በመሆኑ በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እና የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ አጀንሲ በጋራ ጥናት በማድረግ የተለዩ ክፍተቶችና እና የቤት ሽያጭ ዋጋ ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። የተደረገ ማሻሻያ አሰራር ሥርዓት ሆኖ እዲቀጥል እና አገልግሎት አሰጣጡን እንዲያሳልጥ ይህ ማኑዋል ወጥቷል ።

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ማህደርና ሪከርድ

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እና የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቤት ሽያጭ ዋጋ ተመን አሰራር ማንዋል ቁጥር 001/2016 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የታሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ማንዋል ውስጥ፡-

1. ቢሮ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ነው I
2. ኤጀንሲ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ነው I
3. የቤት ሽያጭ ዋጋ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ ቤት ወቅታዊ አማካይ የገበያ ዋጋ ተብሎ በተቋማቱ በጋራ የተጠና ወይም የተወሰነ ዋጋ ማለት ነው።
4. የቦታ መገኛ ዋጋ/ location value / ማለት በዚህ ማኑዋል መሰረት በከተማው አስተዳደር ለተጠና የቦታ ደረጃ የተሠጠ የአንድ ካሬ ወቅታዊ የሊዝ ጨረታ አማካይ ዋጋ ማለት ነው።
5. የነጠለ ግንባታ ዋጋ ማለት በዚህ ማኑዋል መሰረት ለቤት ግንባታ ለአንድ ካሬ የተሰጠ ዋጋ ማለት ነው።

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

6. ኮንደሚንየም ማለት በዚህ ማኑዋል ትርጉም በከተማ አስተዳደሩ ለመኖሪያ ወይም ቅይጥ አገልግሎት ተገንብቶ የጋራ ይዞታ ኖሮት በተነጻጸር ካርታ የተያዘ ቤት ማለት ነው።
7. አፓርትሜንት ማለት በዚህ ማኑዋል ትርጉም ለመኖሪያ ወይም ቅይጥ አገልግሎት ተገንብቶ የጋራ ይዞታ ኖሮት በተነጻጸር ካርታ የተያዘ ቤት ማለት ነው
8. ሌሎች ግንባታዎች ማለት ከኮንደሚንየም እና አፓርትሜንት ውጪ ያሉ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ቤት ወይም ህንጻ ማለት ነው።

3. ተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ ማኑዋል ተፈፃሚ የሚሆነው፡- በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ቤቶች ወይም ህንጻዎች በመሬት ልማትና አስተዳደርና የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በሽያጭ የሚቀርቡ የሰም ንብረት ዝውውር አገልግሎት ጥያቄዎች ላይ ነው።

ክፍል ሁለት

4. የቤት ሽያጭ ዋጋ ግምት

የተሻሻለው የቤት ሽያጭ ዋጋ እና ለሰመ ንብረት ዝውውር የሚከፈሉ ክፍያ ስሌት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. ሌሎች ግንባታዎች (ከኮንደሚንየም እና አፓርትመንት ዉጪ) ለሆኑ የቀረበ ማሻሻያ

በሰኔ 8/2015 ተግባራዊ የተደረገው ወቅታዊ የቤት ሽያጭ ዋጋ ላይ ሌሎች ግንባታዎች (ከኮንደሚንየም እና አፓርትመንት ዉጪ) ለሆኑ ይዞታ የቀረበ ማሻሻያ ዋጋ፡-

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

ሀ) የግንባታ ነጠላ ዋጋ በጭቃ የተሰራ ቪላ ቤት (G+0) ነጠላ ዋጋ በካሬ 15,000 ብር ፣ በብሎኬት የተሰራ የቪላ ቤት (G+0) ነጠላ ዋጋ በካሬ 20,000 ብር ፣ የህንጻ ወለላቸው ከG+1 እስከ G+5 25,000 ብር እና G+6 እና በላይ የሆኑ ቤት ወይም ህንጻ ነጠላ ዋጋ በካሬ 30,000 ተደርጓል።

ለ) የቦታው መገኛ ዋጋ /location value/ ለከተማው የቦታ ደረጃ የጸደቀው ወቅታዊ አማካይ የሊዝ ጨረታ ዋጋ እንዲሆን ተደርጓል።

ሰንጠረዥ 1. ሊሉኞ ግንባታዎች (ከኮንደሚንየም እና አፓርትመንት ዉጪ) ለሆኑ የቀረበ ማሻሻያ

ተ/ቁ	የቦታ ደረጃ	location value/የቦታው መነሻ ዋጋ	የግንባታ ነጠላ ዋጋ በካሬG+0 የሚቃ	የግንባታ ነጠላ ዋጋ በካሬG+0 የብሎኬት	የግንባታ ነጠላ ዋጋ በካሬ G+1-G+5	የግንባታ ነጠላ ዋጋ በካሬ G+6 እና በላይ
1	1/1	39,073	15,000	20,000	25,000	30,000
2	½	36,826	15,000	20,000	25,000	30,000
3	1/3	34,578	15,000	20,000	25,000	30,000
4	¼	31,119	15,000	20,000	25,000	30,000
5	1/5	29,096	15,000	20,000	25,000	30,000
6	2/1	27,074	15,000	20,000	25,000	30,000
7	2/2	25,051	15,000	20,000	25,000	30,000
8	2/3	23,028	15,000	20,000	25,000	30,000
9	2/4	21,005	15,000	20,000	25,000	30,000
10	2/5	18,983	15,000	20,000	25,000	30,000
11	3/1	16,960	15,000	20,000	25,000	30,000
12	3/2	14,937	15,000	20,000	25,000	30,000
13	3/3	12,914	15,000	20,000	25,000	30,000
14	¾	10,892	15,000	20,000	25,000	30,000
15	3/5	8,869	15,000	20,000	25,000	30,000
16	4/1	6,846	15,000	20,000	25,000	30,000
17	4/2	4,823	15,000	20,000	25,000	30,000
18	4/3	2,801	15,000	20,000	25,000	30,000

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

በመሆኑም ቀመሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

$$ሀ = (ለ \times ሐ) + (መ \times ሠ)$$

ሀ ፡ የንብረቱ ጠቅላላ የሽያጫ ዋጋ

ለ ፡ ለአንድ ካሬ የተሰጠ የግንባታ ነጠላ ዋጋ

ሐ ፡ አጠቃላይ የግንባታ ስፋት በካሬ (total floor area)

መ ፡ የቦታው መነኛ አማካይ ዋጋ (Location Value)

ሠ ፡ የይዞታዉ/የቦታዉ/ ጠቅላላ ስፋት (total area of land)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማህደርና ሪከርድ

5. ለኮንዶሚኒየም ቤቶች

በቀን 8/10/2015 ዓ.ም ለኮንዶሚኒየም ቤቶች አማካኝ የሽያጭ ዋጋ ላይ 34% በመቀነስ የተደረገ ማሻሻያ ነው።

ሰንጠረዥ2. ለኮንዶሚኒየም ይዞታዎች

ተ/ቁ	የቦታ ደረጃ	የአንድ ካሬ ዋጋ
1	1/1	47,769
2	½	46,079
3	1/3	44,099
4	¼	42,779
5	1/5	41,672
6	2/1	41,012
7	2/2	39,362
8	2/3	38,042
9	2/4	36,722
10	2/5	35,317
11	3/1	34,657
12	3/2	33,337
13	3/3	32,017
14	¾	30,697
15	3/5	30,037
16	4/1	28,717
17	4/2	26,400
18	4/3	25,080

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

በዚህም መሰረት፡-

$ሀ = ጠ \times ሐ$

ሀ ፡ የንብረቱ ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ

ጠ ፡ የአንድ ካሬ ዋጋ

ሐ ፡ አጠቃላይ የግንባታ ስፋት በካሬ (total floor area)

፩. ለኢንቨስትመንት ይዞታዎች የተቀመጡ አማራጭ ሀሳቦች

በቀን 8/10/2015 ዓ.ም ለኢንቨስትመንት ቤቶች አማካኝ የሽያጭ ዋጋ ላይ 34% በመቀነስ የተደረገ ማሻሻያ ነው።

ሰንጠረዥ3. የኢንቨስትመንት ቤቶች የአንድ ካሬ ዋጋ

ተ/ቁ	የቦታ ደረጃ	የአንድ ካሬ ዋጋ
1	1/1	81,798
2	1/2	79,158
3	1/3	77,178
4	1/4	75,198
5	1/5	64,215
6	2/1	63,555
7	2/2	62,235
8	2/3	60,915
9	2/4	59,595
10	2/5	56,760
11	3/1	56,100
12	3/2	54,120
13	3/3	52,800
14	3/4	51,480
15	3/5	50,820
16	4/1	49,500
17	4/2	48,840
18	4/3	48,180

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

በመሆኑም ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ ቀመሩ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

$$ሀ = ጠ \times ሐ$$

ሀ ፡ የንብረቱ ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ

ጠ ፡ የአንድ ካሬ ዋጋ

ሐ ፡ አጠቃላይ የግንባታ ስፋት በካሬ (total floor area)

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማህደርና ሪከርድ

7. በውርስ የተገኘ ይዞታ የስመ ንብረት ዝውውር

1. በውርስ የተገኘ ይዞታን የስመ ንብረት ዝውውር በተመለከተ ለቪላ ቤቶች የአንድ ካሬ የግንባታ ነጠላ ዋጋ 10,000 ብር ሲሆን ከአንድ ወለል በላይ የሆኑ ግንባታዎች የአንድ ካሬ የግንባታ ነጠላ ዋጋ 12,000 ብር ይሆናል።

ክፍል ሶስት

የታክስ እና የአገልግሎት ክፍያዎች፤

8. ለመኖሪያ አገልግሎት የዋሉ ይዞታ ሰም ዝዉዉር ክፍያዎች፡

የመኖሪያ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ቤት የስም ዝውውር ለማድረግ ከዚህ በታች የተመለከቱት የታክስና የአገልግሎት ክፍያዎች እንደየአግባብነታቸዉ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

1. የቴምበር ቀረጥ ከጠቅላላው ዋጋ ----------2%፣
2. የአሹራ ክፍያ ከጠቅላላው ዋጋ ----------4%፣
3. የማህደር ማጣሪያ----------800 ብር
4. የባለቤትነት መመዝገቢያ----------1000 ብር
5. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የማይተመን ከሆነ----------1000 ብር
6. የመሀንዲስ አገልግሎት እንደ ቦታዉ ስፋት መጠን የተቀመጠውን ክፍያ ሲፈጸም አገልግሎቱ ይሰጣል።

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

9. ከመኖሪያ ውጪ ወይም ለጥምር አገልግሎት የሚሰጡ (ለንግድ ወይም ለመኖሪያና ንግድ) ይዞታዎች የስም ዝውውር ክፍያዎች፡

በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ላይ የተገለጸዉ የቤቱ አገልግሎት ንግድ ወይም መኖሪያና ንግድ የሚል ሆኖ ባለፉት ሁለት ዓመታት ጊዜ ዉስጥ ለንግድ አገልግሎት መዋሉ በወረዳዉ ወይም በክ/ከተማዉ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ሲረጋገጥ እና ለንግድ አገልግሎት የዋለው ቤት ስፋት ከጥቅላላው 30 በመቶ በላይ ሲሆን፡-

1. የቴምበር ቀረጥ ከጠቅላላ ዋጋ----------2%፣
2. የአሹራ ክፍያ ከጠቅላላ ዋጋ ----------4%፣
3. የካፒታል ዕድገት ታክስ ክፍያ ከሚመከተው ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ክፍያ ስለመፈጸሙ ወይም መክፈል እንደማይገባው ማስረጃ ሲቀርብ፣
4. የባለቤትነት መመዝገቢያ ----------1000 ብር፣
5. የማህደር ማጣሪያ----------1000 ብር

6. አዲስ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚታተም ከሆነ----------1000 ብር
7. የመሆንዲስ አገልግሎት እንደ ቦታዉ ስፋት መጠን የተተመጠጠን ክፍያ ሲፈጸም አገልግሎቱ ይሰጣል።
8. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ላይ የተገለጸው የቤቱ አገልግሎት ለድርጅት ወይም ለመኖሪያና ንግድ የሚል ከሆነና እያገለገለ ያለው ለባለቆት ሁለት ዓመታት ለመኖሪያ አገልግሎት መሆኑ በወረዳው ንግድና ኢንደስትሪ ጽ/ቤት ከተረጋገጠ የካፒታል እድገት ግብር አይከፍልም።
9. ከመንግስት ወደ ግለሰቦች በሽያጭ የተላለፉ የድርጅት ይዞታዎች ላይ የካፒታል ዕድገት ታክስ አይከፈልበትም። ሌሎች ክፍያዎች ግን ተግባራዊ ይደረጋሉ።
10. በፍርድ ቤት በተደረገ የባለይዞታ የስም ለውጥ ወይም በይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ላይ የትዳር አጋር ስም ሲካተት ወይም በእነ ስም ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ባለይዞታዎች ስም የተሰጠ ሆኖ የሁሉም ባለይዞታዎች ስም በዝርዝር እንዲካተት ሲደረግ ወይም የንግድ ድርጅቶች የአክሲዮን አባላት ለውጥ ሳይኖር በፍርድ ቤት ወይም በውልና ማስረጃ የጸደቀ የንግድ ድርጅቱ የስም ለውጥ ቢደረግ የአሸራ፣ የቴምብር ቀረጥ እና የካፒታል እድገት ክፍያዎች አይከፍሉም።
11. ከላይ በተራ ቁጥር 10 የተገለጸው ቢኖርም የንግድ ድርጅቶች የአክሲዮን አባላት ለውጥ ካለ የአሸራ፣ የቴምብር ቀረጥ እና የካፒታል እድገት ክፍያዎች እንደ አግባቡ ሊከገል ይችላል።

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

12. ምትክ ቦታ የተሰጣቸው የልማት ተነሺዎች በቦታው ላይ ግንባታ ባያሳርፉም በውርስ ማስተላለፍ ሲፈልጉ ይዞታቸው በቀድሞ በተከፈላቸው የካሳ ክፍያ ስሌት መሰረት በማድረግ የስም ዝውውሩ ተሰልቶ የአሸራ እና የቴምብር ቀረጥ ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል።
13. ነባር ይዞታዎች በሽያጭ ወይም በስጦታ ወደ ሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ ወይም በባለይዞታው ፍላጎት ወደ ሊዝ ስሪት ለመግባት ጥያቄ ሲያቀርብ በሊዝ አዋጁ እና ደንብ መሰረት ለቦታ ደረጃው የተተመጠውን የሊዝ መነሻ ዋጋ ይከፈላል።
14. በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ስልጣን ባለው አካል በሚሰጥ ውሳኔ ለሚቀርብ የስም ዝውውር ጥያቄ ከክፍያ ነጻ ይደረጋሉ።
15. በምደባ ወይም በፈቃደኝ ግንባታ ሳይከናወን በውርስ ለሚተላለፍ ይዞታ በተከፈለው የሊዝ ቅድመ ክፍያ ስሌት መሰረት በማድረግ የስም ዝውውሩ ተሰልቶ የአሸራ እና የቴምብር ቀረጥ ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል።

10. ለይዞታና ቤት ባለቤትንት ማረጋገጫ ካርታ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ

1. በጨረታ፣ በምደባ እና በምትክ ለተላለፉ ቦታዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚወሰን የመሀድስና አገልግሎት ክፍያ እንደ ቦታው ስፋት የሚወሰን ይሆናል
2. ለካርታ ኮፒ/ምትክ ካርታ ----------2500 ብር፣
3. በይዞታ ማካፈል ወይም መቀላቀል ወይም የተናጥል ካርታ ሲሰጥ ለአዲሱ ካርታ ------ 1000 ብር

11. የተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎች
    1. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ላላቸውም ሆነ ለሌላቸው ሰነድ ለማጣራት ------- 1000 ብር
    2. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሕጋዊነት የማረጋገጥ (ጀርባ ማህተም) አገልግሎት ..... 1100 ብር፣
    3. የመስክ ልኬት የሚደረግ ከሆነ እንደ ቦታው ስፋት የመሀንዲስ ክፍያ ከታች በዝርዝር በቀረበው መሰረት የሚከፈል ይሆናል።
    4. የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ (ካርታ) ለጠፋባቸው በጋዜጣ ማስታወቂያ ለማስወጣት--- --- 1000 ብር
    5. ለዋስትና ምዝገባ አገልግሎት ---------- 2500 ብር
    6. ዋስትና ስረዛ አገልግሎት ---------- 2500 ብር
    7. ዕዳና ዕገዳ ምዝገባ አገልግሎት ---------- 1000 ብር
    8. ዕዳና ዕገዳ ስረዛ አገልግሎት ---------- 1000 ብር
    9. በባንክ ጥያቄ ለሚቀርብ የማህደር ሙሪዳ ማጣራት አገልግሎት------1000 ብር
    10. አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አገልግሎት ------- 1100 ብር
    11. ለሀራጅ ትዕዛዝ ባለሙያ መላክ ---------- 1100 ብር
    12. ወሰን የማመላከት አገልግሎት

ለመሀንዲስ አገልግሎት በአንቀጽ 44 በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት እንደ ቦታ ስፋቱ፣

13. ከማህደር የሰነድ ኮፒ ጥያቄ
    ሀ. ለአንድ ገጽ ሰነድ ---------- 50 ብር
    ለ. ከአንድ ገጽ በላይ ለሚቀርብ ጥያቄ ለመጀመሪያው ገጽ 50 ብር በተጨማሪ ለአያንዳንዱ ሰነድ 5 ብር፣

12. ለአገልግሎት ለውጥ የሚከፈል ክፍያ
    1. ከንግድ ወይም ቅይጥ አገልግሎት ወደ መኖሪያ አገልግሎት ---------- 5000 ብር
    2. ከመኖሪያ አገልግሎት ወደ ንግድ ወይም ቅይጥ አገልግሎት---------- 1000 ብር

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

13. ለፍትህ ብሄር ክርክሮች ለሚሰጥ ምላሽ የሚከፈል ክፍያ

1. ለፍ/ቤት ምላሽ ማስረጃ ለማጣራት ---------- 1000 ብር
2. ለፍ/ቤት ምላሽ የልኬት ስራ የሚከናወን ሲሆን በቦታ ስፋት፡-
   ሀ. እስከ 100 ካ.ሜ------- 500 ብር
   ለ. ከ100 ካ.ሜ በላይ እስከ 500 ካ.ሜ ---------- 1000 ብር
   ሐ. ከ500 ካ.ሜ በላይ እስከ 1000 ካ.ሜ ---------- 3000 ብር
   መ. ከ1000 ካ.ሜ በላይ እስከ 10000 ካ.ሜ ------- 5000 ብር
   ሠ. ከ10,000 ካ.ሜ በላይ እስከ 50,000 ካ.ሜ ----- 8000 ብር
   ረ. ከ50,000 ካ.ሜ በላይ 100000 ካ.ሜ ---------- --10000 ብር
   ሰ. ከ100,000 ካ.ሜ በላይ ---------- 20,000 ብር

14. ከፍትህ/ብሄር ክርክር በስተቀር የመሰክ ልኬት ለሚደረግላቸው አገልግሎቶች እንደ ቦታው ስፋት የመሀንዲስ አገልግሎት ክፍያ እንደሚከተለው ይፈፀማል፡-

1. እስከ 100 ሜ/ካ.....ብር 1000
2. 100 በላይ እስከ 500 ሜ/ካ.....ብር 1500
3. 500 በላይ እስከ 1000 ሜ/ካ ..... ብር 4000
4. 1000 በላይ እስከ 10,000 ሜ/ካ ..... ብር 5000
5. ከ10,000 በላይ እስከ 50,000 ሜ/ካ..... ብር 9000
6. ከ50,000 ባለይ እስከ 100,000 ሜ/ካ ..... ብር 15000
7. በ[illegible] ሜ/ካ ..... ብር 25000

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

15. በውርስ ስለሚተላለፍ ከመኖሪያ ውጪ ለተያዘ ይዞታ የካፒታል ዕድገት ታክስ አይከፍልም።

16. መብት ለሚፈጠርላቸው ባለይዞታዎች የሊዝና አገልግሎት ክፍያ ሁኔታ

1. በሊዝ መስተንግዶ የሚሰጣቸው ባለይዞታዎች በሊዝ ደንቡ መሰረት የሊዝ ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል።
2. የይዞታ ማኅተት መስተንግዶ የሚሰጠው በመሬት ይዞታ መብት ፈጠራና ይዞታ አገልግሎት ደንብ ቁጥር 163/2016 እና በሊዝ ደንብ ቁጥር /2016 መሰረት የሊዝና የትጣት ክፍያዎችን የሚከፍል ይሆናል።
3. ለስም ዝውውር የሚከፈል ክፍያ ሲኖር የእሱራ እና የቴምብር ቀረጥ ክፍያዎች የሚከፈል ይሆናል።

17. ሌሎች ክፍያዎች፡-

1. ለአዲስ ካርታ ህትመት ------- ብር 1100
2. የማህደር ማጣሪያ----------ብር 800
3. የባለቤትነት መመዝገቢያ---------ብር 1000



የተሸናና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሀኔች

1. ከሰኔ 8/2015 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ የቤት ሽያጭ ዋጋ ተመን አሰራር
2. ከቤት ሽያጭ ዋጋ ተመን ጋር በተያያዘ ይህ ማኑዋል ከመውጣቱ በፊት የተጸፉ ሰርኩላሮች እና ደብዳቤዎች
3. በዚህ ማኑዋል በልተጠቀሰ ጉዳዮች ላይ የይዞታ አገልግሎትና መብት ፈጠራ ደንብ መሰረት ይፈጸማል።

አቶ ሲሳይ ጌታቸው
የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማህደርና ሪከርድ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

City Government of Addis Ababa Land
Development & Administration Bureau

ቁጥር አአ/መል/አ/ቢ 01/9232/2016 ቀን 12/12/2016 Ref.No
Date

ለአራዳ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለጉላሌ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለልደታ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለቂርቆስ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለኮልፌ ቀራንዮ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለንፋስ ስልክ ላፍቶ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለአቃቂ ቃሊት የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለቦሌ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለየካ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለሚኩራ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለአዲስ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ADDIS ABABA LAND INFORMATION SERVICE

ጉዳዩ፡- የለፋዓይ ማንዋል መላክን ይመለከታል

የአዲስ አባበ ከተማ የቤት ግብይት ዋጋ ወቅታዊ በማድረግ በቀን 8/10/2015 በደብዳቤ ቁጥር አአ/መልአቢ/01/10970/2015 ከመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በተጻፈ ደብዳቤ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል። ወቅታዊ በተደረገው የቤት ሽያጭ ዋጋ ላይ ከሀብረተሰቡ እና ከተገልጋዩ የሚነሱ ቅሬታዎችን መነሻ በማድረግ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እና የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በጋራ ጥናት በማካሄድ የቤት ሽያጭ ዋጋ ላይ ማሻሻያ ተደርጓል።

በመሆኑም በመሬት ይዞታ መብት ፈጠራና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 የቤት ስመ ንብረት ዝውውር ክፍያ ማለትም አሹራ 4% እና የቴምብር ቀረጥ 2% ከጠቅላላ የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ተሰልቶ ከዛሬ ቀን ጀምሮ ማለትም 17/07/2016 ዓ.ም እንዲከፈል እያሳወቅን ይህንንም ለማስፈፀም የተዘጋጀውን የቤት ሽያጭ ዋጋ ተመን አሰራር እና የታክስና አገልግሎት ክፍያ ማንዋል ቁጥር 01/2016 ዓ.ም 13 ገፅ አያይዘን የላክን መሆኑን እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

☎ +251-011-1565657/0111570883/ 01118550095 ✉ 356/2445 Email:addisababalan d@gmail.com
Facebook፡- Addis Ababa City Land Development Administration Bureau
መልስ በሚጽፉልን ጊዜ እባክዎን የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ
PLEASE QUOTE OUR REF NO WHEN REPLYING
ማገልገል ክብር ነው!
በትንንትና በታማኝነት ህዝብን ማገልገል ደማሞ ድርብ ክብር ነው!!